# አጀንዳ ቁጥር 13

## በመሠረታዊ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ኢዴአፓ-መድህን ያለውን አቋም መገምገም

በዚህ ጥቅል አጀንዳ ላይ የውይይት መድረኩ ግምገማ ለማድረግ ባደረገው ሙከራ በቅድሚያ በአገሪቱ የፖለቲካ መድረክ አከራካሪ የሆኑት ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች የትኞቹ መሆናቸውን ለመለየት ሞክሯል፡፡ በዚህም መሠረት ሁሉም በአገሪቱ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቢያንስ በመርህ ደረጃ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚን የሚቀበሉ ቢሆንም- መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረውን ሚና፣የእርሻ መር ኢኮኖሚና የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ በተመለከተ በመካከላቸው መሠረታዊ ልዩነቶች እንዳሉአቸው በማመን ጉዳዮቹን በተናጠል እንደሚከተለው ለመገምገም ሞክሯል፡፡

## 1. የመንግሥት ሚና በገበያ ኢኮኖሚ

የነፃ ገበያ ወይም የገበያ ኢካኖሚ በአሁኑ ወቅት በአብዛኛዎቹ የአለም አገራት ጥቅም ላይ የዋለና ለአሮች የኢካኖሚ እድገት የተሻለ አማራጭ ተደርጎ የሚታይ በመሆኑ በእኛም አገር ገዥውም ፓርቲ ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ይህንኑ አቋም ሲያራምዱ ይታያሉ፡፡ ሁሉም በአገሪቱ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያራምዱትን አቋም በዚህ መድረክ ላይ መገምገም አስቸጋሪና የማይቻል በመሆኑ መድረኩ በገዥው ፓርቲና በኢዴአፓ-መድህን መካከል ርዕሰ ጉዳዩን በተመለከተ ያለውን አንድነትና ልዩነት መሠረት በማድረግ ግምገማውን ለማካሄድ ሞክሯል፡፡

> የገበያ ኢኮኖሚን በመርህ ደረጃ በመቀበል ረገድ በገዥው ፓርቲና በኢዴአፓ-መድህን መካከል የሚታይ ልዩነት የለም፡፡ ነገር ግን ገዥው ፓርቲ በአሁኑ ወቅት እያራመደው ከሚገኘው አቋምና እያከናወናቸው ከሚታዩ ኢኮኖሚያዊ ተግባራት አንፃር በመነሳት ሁለቱ ፓርቲዎች በአፈፃፀም እረገድ በተለይም በገበያ ኢካኖሚ ውስጥ አንድ መንግሥት የሚኖረውን ሚና በተመለከተ መሠረታዊ ልዩነቶች እንዳሏቸው መረዳት ይቻላል፡፡

ኢህአዴግ እራሱን "ልማታዊ መንግሥት" ብሎ በመጥራት ስለልማታዊ መንግሥት በተለያዩ መድረኮች የሚሰጣቸውን ትንታኔዎች ስናደምጥ ምን ያህል ከገበያ ኢኮኖሚ ጋር የማይጣጣም አቋም እንዳለው ለመረዳት እንችላለን፡፡ ይኸውም ለኢህአዴግ ልማታዊ መንግሥት ማለት መንግስት ለገበያ ውድድር የተመቸ ሁኔታ በመፍጠር እረገድ ብቻ ሳይሆን እራሱን በገበያው ውስጥ ተወዳዳሪ በማድረግም ጭምር አገርን የልማት ከፍተኛ ድርሻ አለው ብሎ ማመን ነው፡፡ በኢህአዴግ እምነት አብዛኛው የግል ክፍለ ኢካኖሚ የኪራይ ሰብሳቢነት ሚና ያለው በመሆኑ አገሪቱን በማልማት የማሳደጉ ዋና ድርሻ የሚጠበቀው ከመንግሥት ነው፡፡ ስለሆነም መንግሥት ይህንን ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ በኢካኖሚው ውስጥ የሚኖረው ድርሻ ትልቅና ጠንካራ መሆን አለበት ማለት ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ይመስላል በአሁኑ ወቅት በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ሊሸፈኑ የሚችሉና ወደ ግል ይዞታነት ሊዛወሩ ከሚገባቸው በመንግሥት ይዞታ ስር ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች ውስጥ መንግስት ትርፋማ ያልሆኑትን ብቻ እየመረጠ ሲሸጥ የሚታዬው፡፡

በኢዴአፓ-መድህን እምነት ልማታዊ መንግሥት መሆን በጥቅሉ የሚደገፍ አስተሣሰብ ቢሆንም ለአንድ አገር የልማት እድገት ትልቁ ድርሻ የመንግሥት ነው ብሎ ማመን ግን ትክክለኛ ያልሆነና ከመሠረታዊ የገበያ ኢካኖሚ አስተሳሰብ ጋር የማይጣጣም አቋም ነው፡፡ በኢዴአፓ-መድህን እምነት እንደ ኢትዮጵያ ገና ከእዝ ኢኮኖሚ ወጥተው ወደገበያ ኢካኖሚ በመሸጋገር ላይ ባሉ አገሮች በግሉ ክፍለ ኢካኖሚ በቂ የገበያ ውድድር ባልተፈጠረባቸው የኢካኖሚ መስኮች የመንግሥት ጊዜያዊ ተሳትፎ መኖሩ አማራጭ የሌለውና የሚደገፍ ቢሆንም ከዚህ ውጭ በሆነ ማንኛውም ሁኔታ መንግሥት የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ የሚተካ ድርሻ ሊኖረው

አይገባም፡፡ የመንግሥት ጥረት በአንድ በኩል የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚና የገበያው ውድድር ሊሸፍናቸው ያልቻሉ ክፍተቶችን መሙላትና በሂደት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረውን ድርሻ ለግሉ ክፍለ ኢካኖሚ እየለቀቀ መሄድ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በገበያ ኢካኖሚው ውስጥ ፍትሃዊ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል የሕግና የአፈፃፀም ስርዓት በመዘርጋት የኢኮኖሚው እድገት አገርና ሕዝብ ጠቀም እንዲሆን ማስቻል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዋናው የመንግሥት ኃላፊነት እራሱን ነጋዴና ተፎካካሪ ማድረግ ሳይሆን የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ የበለጠ በማጠናከር በዚያው መጠን የታክስ መሠረቱን የበለጠ ማስፋትና ከዚያ በሚገኝ ገንዘብ በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ሊሸፈኑ የማይችሉ የመሠረተ ልማት አውታሮችን መዘርጋትና መገንባት ነው፡፡

ነገር ግን በአሁኑ ወቅት መንግሥት በልማታዊ መንግስትነት ስም እራሱን ዋና የልማት ወኪል አድርጎ መቁጠሩ፤ በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ሊሸፈኑ የሚችሉ አንዳንድ የልማት ድርጅቶችን በእጁ ይዞ ለመቀጠል መፈለጉ፤ የግሉን ክፍለ ኢካኖሚ እንደ ዋና የልማት ወኪል ሳይሆን አብዛኛውን ጊዜ "ኪራይ ሰብሳቢ" አድጎ የማየት አዝማሚያ ማንፀባረቁ፤ ከዚህም ሁሉ በላይ በኢንዳውመንት ስም የፖለቲካ ፓርቲዎች በኢኮኖሚው ውስጥ የእጅ አዙር ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረጉ ስለ ነፃ የገበያ ኢካኖሚ ያለው አስተሳሰብና አቋም ምን ያህል የተዛባና በችግሮች የተሞላ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

የውይይት መድረኩ መንግስት በገበያ ኢኮኖሚው ውስጥ ሊኖረው ስለሚገባው ድርሻ ባደገው የማጠቃለያ ውይይት በአሁኑ ወቅት ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር የክርክር ነጥብ መሆን የሚገባው መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ተሳትፎ ይኑረው ወይስ አይኑረው የሚል ሳይሆን ምን ያህል ይኑረው የሚለው ነጥብ መሆን እንዳለበት፤ አሁን ካለው የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታም አንፃር መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ውስን ተሳትፎ በሂደት የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ የሚተካ ሳይሆን የበለጠ የሚያጠናክር መሆን እንዳለበት፤ ይህም በተግባር ሊረጋገጥ የሚችለው መንግስት በእጁ የሚገኙ የልማት ድርጅቶች ትርፋማም ይሁኑ አክሳሪ በግሉ ኢኮኖሚ ሊሸፈኑ የሚችሉ እስከሆነ ድረስ በፍጥነት ወደ ግል ይዞታነት እንዲሸጋገሩ በማድረግና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የፖለቲካ ድርጅቶች በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ በማስቀም እንደሆነ ግምገማው አምኖበታል፡፡ መንግስት ይህንን አይነት እርምጃ በተግባር መውሰድ ካልቻለና እራሱን ከግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ በላይ የልማት ወኪል አድርጎ ማየቱን ከቀጠለ ግን የሚያራምደው የኢኮኖሚ ፖሊሲ በተግባር ቅይጥ ኢኮኖሚ እንጂ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሊባል እንደማይችል፣ እንዲህ አይነቱ የመንግስት አቋምም በዋናነት ከኢኮኖሚ ትንታኔ አንፃር ብቻ ሣይሆን "ፖለቲካውን ለመቆጣጠር ኢካኖሚውን መቆጣጠር" ከሚል ፀረ ዴሞክራሲ የሆነ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ የሚመነጭ እንደሆነም ግምገማው አምኖበታል፡፡

## 2. የእርሻ መር ኢኮኖሚ

በውይይት መድረኩ አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ሌላው ጉዳይ የእርሻ መር ኢካኖሚ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ያለው እንደምታ ነው፡፡ በአንድ አገር ኢካኖሚያዊ እድገት ለማምጣት የካፒታል፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ የቴክኖሎጂና የሰው ኃይል መኖር በዋናነት ወሳኝ መሆኑ ይታመንበታል፡፡ ከዚህ መሠረታዊ ግንዛቤ በመነሳት በአሁኑ ወቅት በስልጣን ላይ የሚገኘው መንግስት በአገራችን በዋናነት የሚገኘው ሀብት መሬትና የሰው ጉልበት በመሆኑ ይህንን ሀብት በአግባቡ ተጠቅሞ ኢኮኖሚያዊ እድገት በአገሪቱ ማምጣት የሚቻለው እርሻ-መር የሆነና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የኢኮኖሚ ስትራቴጂ በመከተል ነው የሚል አቋም ያራምዳል፡፡ በዚህም መሠረት ለአለፉት 17 ዓመታት ከኢንዱስትሪና ከአገልግሎት ዘርፉ በላቀ የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ፣ ከከተሞች በላቀ ደግሞ የገጠሩ ክፍል በአገራችን ልዩ ትኩረት አግኝተው ቆይተዋል፡፡

ለአለፉት 5 ዓመታት የአገሪቱ ኢኮኖሚ ባልተቋረጠ ጥሩ ዝናብና በተለያዩ ሌሎች ምክንያቶች ጥሩ መነሳሳት የታየበት ቢሆንም ወደፊት ቀጣይነቱን የሚያረጋግጥ መሠረታዊ መዋቅራዊ ለውጥ ግን እያሳየ አይደለም፡፡ የአገሪቱ ኢኮኖሚ አሁንም በዋናነት የእርሻ ጥገኛ ሆኖ የቀጠለ

ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከ17 ዓመታት በፊት እንደነበረው አሁንም ከ85% በላይ የሆነው የአገሪቱ ሕዝብ እየተዳደረ የሚገኘው ኋላቀር በሆነ የእርሻ ኢኮኖሚ ነው፡፡ የእያንዳንዱ አርሶ አደር አማካኝ የመሬት ይዞታ ከ0.5 ሄክታር ያነሰ እየሆነ ከመምጣቱም በላይ ይህም በተበጣጠሰ መሬት ላይ የተመሰረተ እርሻ ሙሉ በሙሉ ማለት በሚቻል መጠን የዝናብ ጥገኛ በመሆኑ አገሪቱ ከ17 ዓመት ሂደትም በኋላ በምግብ እህል ምርት እራሷን መቻል አቅጧት በየዓመቱ በሚሊዮኖች የሚራቡባት አገር ሆና ቀጥላለች፡፡ በአጠቃላይ በ17 ዓመታት ውስጥ መሠረታዊ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር በአገራችን እየታየ ባይሆንም ገዥው ፓርቲ አሁንም እርሻ መር የሆነ የኢኮኖሚ አቅጣጫውን አጠናክሮ እንደሚቀጥል እየገለፀ ይገኛል፡፡

በኢዴአፓ-መድህን አስተሳሰብ 85% የሆነው የአገሪቱ ሕዝብ በእርሻ ተዳዳሪ በሆነበት በአሁኑ ወቅት ለእርሻው ክፍለ ኢካኖሚ ተገቢ ትኩረት መስጠት የምርጫ ጉዳይ ብቻ ሣይሆን ግዴታም መሆኑን አምኖ ይቀበላል፡፡ ነገር ግን ይህ አገሪቱ ለብዙ ሺ ዘመናት ጥገኛ ሆና የኖረችበት የእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚ የትኛውንም ያህል ትኩረት ቢሰጠው ዞሮ ዞሮ በመጨረሻ በምግብ እህል እራሳችንን ከማስቻልና ለሌላው የኢኮኖሚ ሴክተርም የራሱን ውስን ድጋፍ ከመስጠት አልፎ አጠቃላዩን ኢኮኖሚ እየመራ አገሪቱን የማሳደግ ሚና ይኖረዋል ተብሎ አይታመንም፡፡

ምክንያቱም በዋናነት መሬትና የሰው ጉልበትን በመጠቀም የሚካሄድ ኋላቀር የእርሻ ልማት ከራሱ አልፎ ለኢንዱስትሪውና የአገልግሎት ዘርፍ እድገት መሠረት የሚሆን ካፒታል ለመፍጠር ይችላል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ የአገራችን ግብርና ለሌሎቹ ክፍለ ኢኮኖሚዎች የካፒታል ምንጭ መሆን ይቅርና ሕዝቡን በቋሚነት በመመገብ ረገድ አስተማማኝ ደረጃ ላይ ለመድረስ ገና ከአስርት ዓመታት ያላነሰ ጊዜና ጥረት የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ ወደዚያ ደረጃ ላይ ለመድረስም በራሱ ከሌሎች ምንጮች የሚገኝ ከፍተኛ የካፒታል ድጋፍን የሚጠይቅ ክፍለ ኢኮኖሚ ነው፡፡ ስለዚህ በምግብ እህል እራስን የመቻል ጉዳይ ለአፍታም ሊዘነጋ የማይገባው አንገብጋቢ ጉዳይ ከመሆኑ አንፃር ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ክፍለ ኢኮኖሚ መሆኑ አጠያያቂ ባይሆንም ግብርናው ተጠናክሮ ሌላውን ክፍለ ኢኮኖሚ በመምራት አገሪቱን ወደብልፅግና ያሸጋግራታል ብሎ ማሰብ ግን የማይቻል እንደሆነ ግምገማው አምኖበታል፡፡

የውይይት መድረኩ የግብርናው ዘርፍ የአገራችን ኢኮኖሚ መሪ መሆን አይችልም ከተባለ የኢንዱስትሪው ወይም የአገልግሎት ዘርፉስ መሪ ሊሆኑ ይችላሉ ወይ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ባደረገው ሙከራም የኢንዱስትሪውና የአገልግሎት ዘርፉም በወቅቱ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ እንዳሉ የማይቆጠሩ ዘርፎች በመሆናቸው ኢኮኖሚውን በቀዳሚነት የመምራት ብቃት ሊኖራቸው እንደማይችል አስምሮበታል፡፡ ስለሆነም ከወቅቱ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታና ከሌሎች አገሮች ተሞክሮም አንፃር ተገቢ የሚሆነው አማራጭ እነዚህን በሁለንተናዊ መልኩ ደካማ የሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች መሪና ተመሪ ከማድረግ ይልቅ ለሁሉም ዘርፎች ተገቢና ተመጣጣኝ ትኩረት በመስጠት ተደጋግፈውና እርስ በእርስ ተመጋግበው የሚያድጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት መሆኑን ግምገማው አምኖበታል፡፡ ብዙዎቹ በአጭር ጊዜ የእድገት እመርታ ማሳዬት የቻሉ አገሮች ተሞክሮ የሚያሣዬውም እድገታቸው በዋናነት ከጥቃቅን ኢንዱስትሪና ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጋር ተያይዞ የመጣ በመሆኑ ለእነዚህ ዘርፎች መስፋፋት መሠረት የሆኑት የአገራችን ከተሞችም ከገጠሩ ያላነሰ የትኩረት ማዕከል መሆን እንደሚገባቸው ግምገማው አመላክቷል፡፡

## 3. የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ

ከዋና ዋና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ውስጥ በገዥው ፓርቲና በኢዴአፓ-መድህን መካከል የሚታዬው አንዱ ልዩነት የመሬት ባለቤትነትን የሚመለከት ነው፡፡ የመሬት ጥያቄ በአገራችን የፖለቲካ መድረክ ቢያንስ ለግማሽ ዘመን ሲቀነቀን የቆዬ ቢሆንም ጥያቄው ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎች የሚያስማማ መልስ ሳያገኝ እስዛሬ ዘልቋል፡፡ የደርግ መንግስት የመሬት ላራሹን ጥያቄ ለመመለስ ባደረገው ጥረት የአገሪቱን መሬት ለአርሶ አደሩ ሕዝብ በማከፋፈል እረዥም እርቀት

የተጓዘ ቢሆንም ከባለቤትነት ጥያቄ አንፃር ግን ችግሩ መፍትሄ ሳያኝ ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የኢህአዴግ መንግስትም በመሬት ጥያቄ ዙሪያ ከደርግ ጋር ተመሳሳይ አቋም ይዞ በመቀጠሉ የመሬት ባለቤትነት የሕዝብ ወይም የዜጎች ሳይሆን የመንግስት ሆኖ ቀጥሏል፡፡ የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ በምርጫ ወደስልጣን በሚመጡ የፖለቲካ ድርጅቶች በቀላሉ እንዳይቀየር በመፈለጉም የአገሪቱ ሕገመንግስት ውስጥ እንዲደነገግ ተደርጓል፡፡ ገዥው ፓርቲ የመሬትን የባለቤትነት ጉዳይ ያለአግባብ በሕገ መንግስቱ ውስጥ እንዲካተት ከማድረጉም በላይ የመሬት የባለቤትነት ጥያቄ ሊቀየር የሚችለው በመቃብሬ ላይ ነው በማለት ከዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የሚቃረን የከረረ አቋም ሲያራምድ ይደመጣል፡፡

የውይይት መድረኩ መሬትን በተመለከተ ገዥው ፓርቲ የሚያራምደውን አቋም መሠረት አድርጎ ባደረገው ግምገማ በቅድሚያ ገዥው ፓርቲ መሬት መሸጥ መለወጥ የለበትም ለሚለው አቋሙ የሚያቀርበውን ምክንያት ለማዬት ሞክሯል፡፡ ገዥው ፓርቲ ከሚያቀርባቸው ምክንያቶች ውስጥ ዋናው መሬት እንዲሸጥ እንዲለዎጥ በሕግ ቢፈቀድ ገበሬው ጊዜያዊ ችግር ሲገጥመው መሬቱን እየሸጠ ወደ ከተማ ይፈናቀላል፤ በዚህም ምክንያት እንዳለፈው ስርዓት ጥቂት ግለሰቦች በአገራችን ዋና የሀብት ምንጭ የሆነውን መሬትን ጠቅልለው የመያዝ እድል ያገኛሉ የሚል ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘም ገበሬው ከመሬቱ ሲፈናቀል ለምርት መቀነስ ምክንያት የሚሆን የጉልበት መባከን ይከሰታል የሚል መከራከሪያም ይቀርባል፡፡

ከእነዚህ የገዥው ፓርቲ መከራከሪያ ነጥቦች በመነሳትም መድረኩ መሬትን በሚመለከት አገሪቱ ልትከተል ስለምትችለው አማራጭ ተወያይቷል፡፡ በቅድሚያ አገሪቱ ውስጥ መሬትን አስመልክቶ የሚነሳው ክርክር መሬት “ይሸጥ-አይሸጥ” ከሚል ጠባብ ክርክር ወጥቶ ከአጠቃላይ የአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅም ጋር ተገናዝቦ በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ አማራጮችን የሚያካትት መሆን እንዳለበት፤ የመሬት ጉዳይ በዋናነት ከፖለቲካ ጉዳይነት ይልቅ የኢኮኖሚ ጉዳይ ሆኖ መታየት እንዳለበት፣ መሬት ከሕገ መንግሥታዊ ጉዳይነት ወጥቶ እንደማንኛውም አማራጭ አጀንዳ በምርጫ አሸናፊ የሚሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕገ መንግሥትን ማሻሻል ሳያስፈልግ የሚዎስኑት ጉዳይ መሆን እንዳለበት ግምገማው አምኖበታል፡፡

ከዚህ መሠረታዊ አቋም በመነሳትም በአጠቃላይ በአገሪቱ ያለው መሬት በመንግሥት ባለቤትነት ተይዞ ይቀጥል ወይም በግለሰብ ባለቤትነት ይያዝ ከሚለው ጠባብ አማራጭ ወጥቶ መሬት በሦስት ዋና ዋና ስሪቶች ማለትም በግል፣ በወልና በመንግስት ባለቤትነት መያዝ እንደሚገባው ታምኖበታል፡፡ ይህም ማለት በአሁኑ ወቅት በአርሶ አደሮች እጅ ተይዞ በእርሻ ጥቅም ላይ የዋለውና ግለሰቦች የድርጅትም ሆነ የመኖሪያ ቤት የገነቡበት የአገሪቱ መሬት የመሸጥ መለወጥ መብትን ባካተተ መልኩ በግል ይዞታነት እንዲያዝ፣ መሠረታዊ የአኗኗር ለውጥ እስከሚፈጠር ድረስ በተለያዩ የአገሪቱ ቆላማ ክፍሎች ከብት አርቢው ሕብረተሰብ ለግጦሽ የሚጠቀምበትና በከተሞች የቤት ስራ ማኅበራት የሰፈሩበት መሬት በወል (በማህበረሰብ) ይዞታነት ተይዞ እንዲቀጥል፣ እስካሁን ሕዝብ ያልሰፈረበት የገጠር መሬትና ግንባታ ያልተካሄበት የከተማ መሬት በሂደት የሕዝቡን ጥቅም በሚያስጠብቅ ሁኔታ ወደ ግል ይዞታነት እስከሚዛወር ድረስ ለጊዜው በመንግሥት ይዞታነት ተይዞ እንዲቀጥል የሚያደርግ ከየአካባቢው ሁኔታ ጋር የተገናዘብ የመሬት ስሪት ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ታምኖበታል፡፡

መሬት እንዲሸጥ እንዲለወጥ በሕግ ቢፈቀድ አርሶ አደሩ በጊዜያዊ ችግር መሬቱን እየሸጠ ወደ ከተማ ሊፈናቀል ይችላል የሚለው የገዥው ፓርቲ ስጋት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ አንድ ስጋት ቢሆንም መሬቱን እንዳይሸጥ እንዳይለውጥ በሕግ መገደብ በአገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ ላይ ሊያስከትል ከሚችለው ጉዳት አንፃር ሲመዘን ግን ስጋቱ ከሚገባው በላይ የተለጠጠና ቁንፅል እይታ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ግምገማው አምኖበታል፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያ ደረጃ እንዲህ አይነቱ አርሶ አደሩ ሕዝብ መሬትን የመሸጥና የመለወጥ

መብት ቢሰጠው ህልውናው የተመሰረተበትን ጥቅም በቀላሉ ለሌላ አሳልፎ ይሰጣል ብሎ ማመን አርሶ አደሩን ህዝብ ጥቅሙን የማያውቅ ሕዝብ አድርጎ የሚፈርጅና ስለጥቅምህ የማውቅልህ እኔ ነኝ የሚል ኢ-ሞራላዊ የሆነ አስተሳሰብ ነው፡፡ ሁለተኛ መሬት መሸጥ መለወጥ የለበትም የሚለው አማራጭ 85% የሆነውን የአገሪቱን አርሶ አደር ሕዝብ ሁልጊዜም ከእጅ ወደ አፍ ከሆነው የእርሻ ኑሮው ተላቆ አዲስ የሕይወት አቅጣጫ ለራሱም ሆነ ለልጆቹ ማየት እንዳይችል የሚገድብና ከዚሁ ጋር በተያያዘም በእርሻ ላይ ጥገኛ የሆነው የአገሪቱ ኢኮኖሚ ወደ ሌሎች ክፍለ ኢኮኖሚዎች መዋቅራዊ ሽግግር እንዳያደርግ አስሮ የሚይዝ አስተሳሰብ ነው፡፡ ሦስተኛ ለገበያና ለመሰረተ ልማት አውታሮች ቅርብ በሆኑ አካባቢዎች መሬትን ገዝተው በተለያዩ መስኮች ልማትን ማስፋፋት የሚፈልጉ ባለሀብቶችን እድል የሚያጠብና የከተሞች አካባቢን መሠረት አድርጎ ሊስፋፉ የሚችልን የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፍ እድገት አዝጋሚ እንዲሆን የሚያደርግ ነው፡፡ አራተኛ መሬት በመንግሥት ባለቤትነት ተይዞ እስከቀጠለ ድረስ የሕዝቡ ቁጥር እየጨመረ በመጣ ቁጥር እንደገና መሬትን የማከፋፈል ፍላጎት መኖሩ ስለማይቀር አርሶ አደሩ በእጁ የያዘውን መሬት እስከመጨረሻው የራሱ እንደሆነ በማመን አስተማኝ እንክብካቤና ጥበቃ ሊያደርግለት አይችልም፡፡ ይህም በራሱ በአካባቢ መራቆት ላይ የራሱ የሆነ ከፍተኛ ተፅእኖ የሚያሳድግ ይሆናል፡፡ አምስተኛ የመሬት እንደገና መከፋፈል ጉዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አስካልቆመ ድረስ አርሶ አደሩ ወደፊት ሊደረግ በሚችለው የመሬት ክፍፍል የተሻለ ድርሻ ለማግኘት ሲል ብዙ ልጆችን ለመውለድ ስለሚገፋፋ ይህም በራሱ በአገሪቱ የሕዝብ ቁጥር ማደግ ላይ ከፍተኛ ጫና ያስከትላል፡፡ በአቃላይም መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ በሕግ በመታገዱ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉትን እነዚህን መሠረታዊ ችግሮች ስናጤናቸው አርሶ አደሩ መብቱ በሕግ ቢገደብም በመጨረሻ መሬቱን እየለቀቀ መሰደድ ብቻ ሣይሆን በያዘውም ቁራጭ መሬት ላይ በቂ ምርት አምርቶ እራሱን የማይችልበት ሁኔታ የበለጠ እየተባባሰ መምጣቱ አይቀሬ ነው፡፡ ይልቁንስ የተሻለ አማራጭ የሚሆነው አርሶ አደሩ ለሺ ዘመናት ጥገኛ ሆኖ ከኖረበት የተራቆተና የተበጣጠሰ መሬት አሁንም ተቆራኝቶ እንዲኖር ማድረግ ሳይሆን በተቻለ ፍጥነት የኢንዱስትሪውና የአገልግሎቱ ዘርፍ እንዲስፋፋ በማድረግ ወደፊት ከእርሻው ክፍለ ኢካኖሚ መፈናቀሉ የማይቀረውን ሕዝብ በበቂ መጠን እንዲያስተናገድ ማስቻል ነው፡፡

ከዚህ ውጭ አርሶ አደሩ ሕዝብ በይዞታው የሚገኘው አማካኝ የመሬት መጠን ከ0.5 ሄክታር እያነሰ በመጣበት ሁኔታ፣ አብዛኛው አርሶ አደርም በዚህ ብጥስጣሽ የመሬት መጠን የአመት ቀለቡን ማምረት የማይችልበት ሁኔታ እየተፈጠሩ ከመምጣቱ አንፃር፣ ከሁሉም በላይ የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ መጠን እየጨመረ በመሄዱ ምክንያት የአገራችን የሕዝብ ቁጥር ከ20 ዓመታት በኋላ ከ150 ሚሊዮን በላይ እንደሚሆን በሚገመትበት በአሁኑ ወቅት እንዲህ አይነቱን የአገሪቱን ችግሮች የበለጠ የሚያባብስ የመሬት ፖሊሲ ማራመድ በምንም አይነት መመዘኛ ትክክለኛ ሊሆን አይችል፡፡ እንደዚህ አይነቱ የመሬት ፖሊሲም ከኢኮኖሚ ትንታኔ አንፃር ትርጉም የሚሰጥ ከመሆኑ ይልቅ ገዥው ፓርቲ መሬትን በእጁ በመቆጣጠር አርሶ አደሩን ሕዝብ የፖለቲካ መጠቀሚያ ለማድረግ እየጣረ ነው የሚውን ትችት የበለጠ የሚያጠናክር ነው፡፡

ከዚህ አጠቃላይ ግምገማ በመነሳትም የውይይት መድረኩ የመሬት ጉዳይ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት መያዙ ቀርቶ በግል፣ በወልና በመንግሥት ባለቤትነት እንደየ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የሚያዝበት አሰራር ቢኖር ለአገሪቱ አጠቃላይ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት እጅግ ጠቃሚ እንደሚሆን አምኖበታል፡፡